ምዕራፍ ፪ ፡

ክፍል ፯ ፡

የአማርኛ ምሳሌ ሁኔታና አፈታት ፤

የአማርኛ ምሳሌ ፡ ማንም ኢትዮጵያዊ ሰው ልዩ ልዩ ጉዳይ ባጋጠመው ጊዜ ሰሚውን በአጭር አነጋገር ለማስረዳት እንደ መልክዓት ዚቅ አድርጎ እየጠቀሰ ፤ የሚገለገልበት ቅኔ ነው ፤ ከዚህም የተነሣ ፡ ምሳሌው ፡ በ፪ ክፍሎች ላይ ይከፈላል ፤ ከነርሱም ውስጥ አንደኛው« ውስጠ - ወርቅ ምሳሌ» ፤ የሚባል ሲኾን ፤ ሁለተኛውም ፡ «ወርቃ - ወርቅ ምሳሌ» ተብሎ ይጠራል ።

ውስጠ— ወርቅ ምሳሌ ።

ውስጠ - ወርቅ ምሳሌ የሚባለው ፡ በወርቅ የሚመሰለው ዋናው ሐሳብ በውስጡ የሚሰማበት ዓረፍተ ነገር ነው ፤ ስለዚህም ምሳሌው ራሱ «ሰም» ሲባል ዋናው ሐሳቡ ደግሞ « ወርቅ » እየተባለ ፤ በኹለት ዓረፍተ ነገሮች ፡ ወይም በሁለት ሐሳቦች ይፈታል ፤

ይሁን እንጂ ፡ አብዛኛው የምሳሌ ወርቅ እንደ ሰሙ በ፩ ሐሳብ ብቻ የተወሰነ አይደለም ፤ ስለዚህ ፡ የምሳሌን ወርቅ በፈለጉት ጾታና ቍጥር እየገለጹ ፡ በብዙ ሐሳቦች ለመፍታት ይቻላል ።
ለምሳሌ ፡

በጊዜ የመጣ እንግዳ ፡ ራቱ ፡ ፍሪዳ ።

ሰም ፡ ተቀባዮቹ ራታቸውን በልተው ሳይተኙ ፤ በጊዜ የመጣ እንግዳ ፡ የሚቀበሉት ሰዎች ፡ እንግዳውን በደስታና በፈገግታ ከመቀበላቸውም በላይ ፡ ፍሪዳ ፡ ታርዶ ፡ ራቱ ፡ በጥሩ አኳኋን ተሰናድቶ ይቀርብለታል ።

ወርቅ ፡ ከሠለጠኑ ወላጆች በመወለድ እንግድነት ወደዚህ ዓለም የመጣ ሕፃን ልጅ ፡ በደስታና በፈግግታ ከሚመለከቱት ወላጆቹ ዘንድ ፡ ተዘጋጅተው የሚጠብቁት የመሰተንግዶ ዓይነቶች ቀዳሚው መልካም አስተዳደግ ሲሆን ፤ ተከታዩ ደግሞ ፡ ዝመናዊ ትምህርት ነው ።

ወርቅ ፡ የትምህርት ጊዜው ሳይተላለፍበት በልጅነቱ የተማረ ሰው ዕውቀቱ የተስፋፋ ፡ ሀብቱ የደረጀ ፡ ኑሮው የተደላደለ ሆኖ ይኖራል ።

ችቦ ፡ ከሼደ ፤ ውሻ ፡ ጮኸ ።

ሰም ፡ ችቦ ፡ የፈለገውን ነገር አድርጎ ከሼደ በኋላ፤ ውሻ ጮኸ ።

ወርቅ ፡ ድኻ ሰው በዚህ ዓለም ላይ ፡ በችግር ሲቄራ መድ ኖሮ ፤ ከሞተ በኋላ ፤ በሕይወቱ ሳለ ፤ ምንም ያልረዳው ሀብታም ዘመዱ ፡ እየጮኸ አለቀሰለት።

ወርቅ ፡ ጠላት ፡ የገደለውን ገድሎ ፡ የቻለውን ያህል ዘርፎ ፡ የማረከውን ማርኮ ፡ እየተቄነነ ካመለጠ በኋላ ፤ ለርዳታ የተላከው ደረሰ ።

ወርቅ ፡ ሴትዮዋ የሆድ ዕቃዋ ነፋስ ድንገት አምልጦ ድምፁን ካሰማ በኋላ ፤ በጣም አፈረችና እግሮች ዋን ሰበሰበች ።

ወርቅ ፡ ሰውዮው ፡ ልበ - ሰፊ ፡ ነገር አሳላፊ ካለመሆኑ የተነሣ ፡ በትንሽ ነገር ተናድዶ ፡ ሰውን በእጁ አጠፋና ፡ ተይዞ ፍርዱን እስቲቀበል ድረስ ፤ ወህኒ ቤት ከገባ በኋላ ፤ አውን በጣም ይጸጸታል ።

ወርቅ ፡ ልጂቷ ፡ በማይረባ ነገር ከባልዋ በተፋታች ጊዜ ፤ ብዙ አማላጆች ተልከው ሲለምኗት ፤ እሻ ፈረኝ ብላ ቀረችና ፡ ባልዋ እርስዋን የምታስንቅ ሚስት አግኝቶ ካገባ በኋላ ፤ አሁን ቁጭቷት ልትሞት ነው ።

የቆጡን አወርድ ብላ ፡ የብብትዋን ጣለች ።

ሰም ፡ ከቆጥ ላይ የተሰቀለውን ነገር አወርዳለሁ ብላ ፡ ወደ ላይ እጅዋን ብታነሣ ፤ በብብትዋ ውስጥ ይዛው የነበረውን ዕቃ ጣለች ።

ወርቅ ፡ ያላትን ንቃ ፡ የያዘችውን አቃልላ ፡ ከዓቅሟ በላይ የሆነውን ነገር ባላት ላይ ለማከል ስትል ፤ ብትንጠራራ ከሁለት ፡ አንዱን ያጣ ሆና ቀረች ።

የምጣዱ ሳለ ፤ የዕንቅቡ ፡ ተንጣጣ ።

ሰም ፡ በጋለው ምጣድ ላይ ያለው እህል እየተቄላ ዝም ብሎ ሳለ ፤ በእንቅቡ ውስጥ ደኅና የተቀመጠው እህል ተንጣጣ ።

ወርቅ ፡ በዚህ ዓለም ላይ ፡ የድኽነት ቀንበር የተጫነው ሰው በችግር ላይ ሳለ ፡ ታግሦና ችሎ ሲኖር ፤ ምንም ነገር ሳይጐድለው በምኞት እየተቀማጠለ የተቀመጠ ሰው ፡ አማረረ ።

ሲሮጡ የታጠቁት ፡ ሲሮጡ ይፈታል ።

ሰም ፡ ሲሮጡ የታጠቁት ሱሪ ፡ ወይም ቀበቶ በሚገባ ስለማይጠብቅ ፤ ደግሞ ሲሮጡ ይፈታል ።

ወርቅ ፡ በችኰላና ባለ ማስተዋል ያደረጉት የጋብቻ

ምሥጢር ፡ መሠረት ስለሌለው ፤ ወዲያው ይፈ
ርሳል እንጂ ፤ አይጸናም ።

አህያ የሌለው ፡ በቅሎ ይንቃል ።

ሰም ፡ ለራሱ ዋጋው አነስተኛ የሆነ አህያ እንኳን የሌ
ለው ሲሆን ፤ ከአህያ የበለጠውን የሰውን በቅሎ
ይንቃል ።

ወርቅ ፡ ለራሱ ሌላው ይቅርና ፊደልን እንኳ ያልቈጠረ
መሃይምን ሲሆን ፤ የምሁር ሰው ሊቅነትን ያቃ
ልላል ።

ወርቅ ፡ ለራሱ በኃጢአትና በተንኰል አዛባ የተጨማ
ለቀ ሲሆን ፤ ንጽሕናውን ጠብቆ ፡ ከማንኛውም
ዓይነት ኃጢአት ርቆ ደኅና የተቀመጠውን ሰው
ስም ሲያጠፉ ይኖራል ።

ፈረስ ፡ ያደርሳል እንጂ ፤ አይዋጋም ።

ሰም ፡ ፈረስ ሽምጥ እየጋለበ ፡ ፈረሰኛውን ፡ ጠላት አለ
በትጋ በቅጽበት ያደርሳል እንጂ ፤ ጥይትን ተኩሶ
ጦርን ወርውሮ ፡ ጐራዴን ሰንዝሮ ፡ ከጠላት ጋራ
አይዋጋም ።

ወርቅ አስተማሪ ስሕተት የሌለውን መግለጫ ጽፎና
አስጽፎ እየገለጸና እያስረዳ ለተማሪው ያስረዳል

እንጂ ፤ በተማሪው ፈንታ ተተክቶ ሌት ተቀን
እያጠና ፤ ብዕሩንና እርሳሱን ይዞ በፈተና ተቀ
ምጦ ጥያቄውን እያነበበ አይፈተንለትም ።

ከቤት ዶሮ ሲታረድ ፤ ከውጪ ቆቅ ፡ ይያዛል ።

ሰም ፡ «ላለው ይጨመርለታል ፤» እንደተባለው ሁሉ ፤
ከቤት ውስጥ ዶሮ ሲታረድ ፤ ከውጪ ደግሞ
ቆቅ ፡ በወጥመድ ይያዛል ።

ወርቅ ፡ ትምህርትና የሥራ ልምምድ ባይኖርም እንኳ ፤
ከግል በኩል ብዙ ሀብትና ርስት ሲኖር ፤ ከሕ
ዝብ ዘንድ መከበርና ዝና ፡ ከመንግሥት በኩል ፡
መታወቅና ሹመት ይገኛል ።

ከዓጋም የተጠጋ ቁልቋል ፡ ሲያለቅስ ይኖራል ።

ሰም ፡ ከዓጋም ተጠግቶ የበቀለው ቁልቋል ፡ ነፋስ ዓጋ
ሙን ባወዛወዘው ቍጥር ፤ በዓጋሙ እሾኽ እየ
ተወጋ ሲደማ ይኖራል ።

ወርቅ ፡ ከክፉ ሰው ጋራ ተጐራብቶ የሚቀመጥ ሰላ
ማዊ ሰው ክፉው ጐረቤቱ በየጊዜው በሚው
ልበት የተንኰልና የምቀኝነት ተግባር ስለሚበ
ሳጭ ፤ ዕድሜ ልኩን እየተመረረ ይኖራል ።

ይህች ባቄላ ፡ ያደረች እንደሆን ፤ አትቁረጠምም ።

ሰም ፡ ይህች ባቄላ ፡ ርሳ ሳለች ፤ አሁኑን መበላት አለባት እንጂ ፤ ካደረችና ከዋለች ዘንድ ፤ በጣም ትደርቅና እሺ ብላ አትቁረጠምም !

ወርቅ ፡ መጥፎ ጠባይን ፡ ሲሆን ከሩቁ ሳለ መጥላት ፡ አለበለዚያም በጣም ሳይለምዱት ፤ ወይም ሥር ሳይሰድ ፤ መተው እንጂ ፤ ከተወሐደና ከተቆራኘ በኋላ ፤ ና ፡ ኺድ ቢሉት እሺ ብሎ አይለቅም !

እጸድቅ ብዬ ባዝላት ፤ ተንጠልጥላ ቀረች !

ሰም ፡ ይገርማል! ስላመማት ፤ ወይም ስለደከማት ፤ እጸድቅ ብዬ ባዝላትና ፤ የቻልኩትን ያህል ተሸክሜ ወስጄ ሳበቃ ፤ እንግዲህ በቃሽ ውረጂልኝ ብላት ፤ «እንቢ አልወርድም» ብላ ከጀርባዬ ላይ ተንጠልጥላ ቀረች !

ወርቅ ፡ ጉድ ነው! የወንድምነቴን ያህል ሰብአዊ ተግባሬን እፈጽማለሁ ብዬ ብረዳት ፤ በሚቻላት መጠን ውለታዬን በመመለስ ፈንታ ፡ የባሰ ጠላት ሆነችብኝና ከራሴ ላይ አልወርድ አለች !

ላለፈው ክረምት ፡ ቤት አይሠራለትም ።

ሰም ፡ እንደ ዓምና ለዘንድሮም እንዳያፈስስ እንጂ ፤ ላለፈው ክረምት ተብሎ ቤት አይሠራለትም ።

ወርቅ ፡ ያልተሠራው ስሕተት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳይሠራ ፡ የተሠራውም በደል ፪ኛ እንዳይደገም እንጂ ፤ ለተፈጸመው ጥፋት ሲባል ጥንቃቄ አይደረግም ።

ዶሮን ሲደልሏት ፤ በመጫኛ ጣሏት ።

ሰም ፡ የበሬን ያህል ጉልበት አለሽ ብለው ዶሮን ሲደልሏት ፡ በመጫኛ ጠልፈው ለመታረድ ጣሏት ።

ወርቅ ፡ ራስዋን የማታውቅ ሩጎጋን ሴት በከንቱ ውዳሴ ሲያሳብዷት ፤ « ከዓለም ቄነጃጅት ሁሉ አንቺ ትበልጫለሽ» ብለው አኩራሯት ።

ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ ፡ አበረኸ ተወቀጥ ።

ሰም ፡ ምንም እንኳ ጣዕምህ ትንሽ የተለየ ቢሆንም ቅሉ ፤ ከኑግ ጋራ ተቀላቅለህ የተገኘህ ሰሊጥ ፤ አብረህ መወቀጥ አለብኽ ።

ወርቅ ፡ ምንም እንኳ ግብረ አበሩ ባትሆንም ቅሉ ፤ ከሌባ ፡ ወይም ከቀማኛ ጋር የተገኘኽ ሰላማዊ ሰው ፡ አብረኽ መደብደብ ፡ ወይም አበረኽ መታሠር አለብኽ ።

ባለቤቱ ያቃለለው አሞሌ ባለ ዕዳው
አይቀበለውም ።

ሰም ፡ ባለቤቱ ያቃለለውንና የናቀውን አሞሌ ፡ ባለ ዕዳው ፡ በቂ ነው ፤ ብሎ አይቀበለውም ።

ወርቅ ፡ ተወላጆቿ የማይተባበሩላት ፡ የማይስማሙላትና የማይቁረቁሩላት ሀገር ፡ የውጪ ጠላት ፡ ታጠቃኛለች ፤ ብሎ ሊፈራት ፡ ትጠቅመኛለች ብሎ ሊያከብራት አይችልም ።

አፍንጫ ሲመታ ፤ ዓይን ያለቅሳል ።

ሰም ፡ በተፈጥሮ አቀማመጥ የተያያዙና የተጋራበቱ በመሆናቸው ፡ አፍንጫ ፡ ሲመታ ፤ ዓይን ፡ ያነባል።

ወርቅ ፡ በሥጋ ልደት የተዛመዱና የተሣሠሩ በመሆናቸው ማንም ሰው ፡ ሲበደል ፤ ዘመዱ ይቀየማል ።

የወደቀ ዛፍ ፡ ምሳር ይበዛበታል ።

ሰም ፡ በአንድ አደጋ ምክንያት ከሥሩ ተመንግሎ የወደቀ ዛፍ ፡ ብዙ ድካምን ስለሚቀንስ ፡ በሱ ላይ ምሳር ይበዛበታል ፤ ማለት ፡ ማንም ምሳር ምሳሩን ይዞ እየቄራረጠ ይጠቀምበታል ።

ወርቅ ፡ በአንድ ምክንያት ተከስሶ ክሹመቱ የተሻረ ሰው ፡ እንደገና ተሹሞ የሚያጠቃ ስለማይመስል ፤ ነቃፊና ጠላት ፡ ከሳሽና ወቃሽ ይበዛበታል ።

እምበላው ሳጣ ፤ልጄ ጥርስ አወጣ ።

ሰም ፡ ለራሴ እምበላውንና እምቀምሰውን ሳጣ ጊዜ ፤ ልጄ ደግሞ ፡ እንጀራ የሚያላምጥበትን አዲስ ጥርስ አወጣ ።

ወርቅ ፡ በፊት የወደቀብኝን አንዱን ችግር ገና ሳልወጣው ፤ አሁን ደግሞ ሌላ ችግር ተደርቦ መጣብኝ ።

የኾብ እንግዳ ፡ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ ።

ሰም ፡ የኾብ እንግዳ ወደማያውቁት አገር ኼዶ ውድቅት ሲሆን ቁርበቱን ተሸክሞ ከቦታው ላይ ጥፍት ለማለት እንዲመቸው ፡ ራሱን ባሕታዊና ጻድቅ በማስመሰል የዋሆች እንግዳ ተቀባዮችን ሰዎች የምተኛበት ነገር ለስላሳውን ሥጋጃ ምንጣፍ ሳይሆን ቁርበትን ብቻ አንጥፉልኝ አለ።

ወርቅ ፡ የሴሰኛ እንግዳ ወደማያውቁት አገር ኼዶ ሰው ሁሉ አምኖ እንዲያስጠጋውና ፡ ከአስጠጋውም

በኋላ ፤ ሳይታወቅበት መጥፎ ሥራውን ለመቀ
ጠል እንዲመቸው «ተሳስቼ ዕድሌን በማበላሸት
ሚስት አግብቼ ዓለማዊ ሰው ሆንኩ እንጂ ፤ የጠ
ባዬስ ሁኔታ ለብሕትውናና ለምንኩስና ኑሮ ብቻ
የተፈጠረ ነበር » ብሎ ለማያውቁት ሰዎች ነገራ
ቸው ።

ከመነኮሰች ባሰች ።

ሰም ፡ የመመንኮስ ዓላማ ከፍሥሐ ወደ ንስሐ ፡ ከሥጋ
ዊነት ወደ ነፍሳዊነት ፡ ከሕያውነት ፡ ወደሙት
ነት ዓለም ለመሸጋገር ሲሆን ፤ እርሷ ግን የተ
ገላቢጦሽ ፡ ከመነኮሰች በኋላ ፤ ከዓለማውያን ሰዎች
ሁሉ ይልቅ አሁን ባሰች ።

ወርቅ ፡ የመማር ዓላማ በተቻለ መጠን ከዱር አራዊት
ነት ወደ ምድር መላእክትነት አኗኗር ለመለ
ወጥ ነበር ፤ ሰው ግን እንደምናየው የዘመኑን ትም
ህርት ተምሮ ሠልጥኗል ፤ ከተባለ ወዲህ ፤ ግርም
ቢጥ በማንኛውም ቁም ነገር ሁሉ ከዱሮው ይልቅ
አሁን የባሰና ያነሰ ሆኗል ።

ያልተገላበጠ ፡ ያራል ።

ሰም ፡ በሰማ ምጣድ ላይ ከተጋገረ በኋላ ፤ በየደቂቃው
እየታየ የላዩን ገጽ ወደታች ፡ የታቹም ወደ ላይ

ሆኖ ያልተገላበጠ የስንዴ ዳቦ ፡ በሸክላው ምጣድ
ግለት ያራል እንጂ ፤ በሚገባ በስሎ መልካም
መብል ሊሆን አይችልም ።

ወርቅ ፡ አንድ ቅጥር ሠራተኛ ፡ ለኑሮውና ለሕይወቱ
ከሚያስብለት ፡ ድካሙንም ከሚያውቅለት መሥ
ሪያ ቤት ፡ በጊዜው እየለቀቀ ፤ የደመወዝ ጭማ
ሪና የማዕርግ እድገት ወደሚገኝበት ቦታ ካልተ
ዛወረ በስተቀር ፤ በሰውነቱ ውስጥ ፡ ብስጭት ፡
በቤቱም ውስጥ ድኽነት ይጨፍርበታል እንጂ ፤
ምንም ቢደረግ አያልፍለትም ።

ከወገንዎችዋ የረዘመች ማሽላ ፡ ወይም ለወፍ ወይም ለወንጭፍ ።

ሰም ፡ አብረዋት ከበቀሉት ማሽላዎች ሁሉ የረዘመች
ማሽላ ፡ ብቻዋን ጐልታ ስለምትታይ ፤ ወይም
ወፍ ይበላታል ፤ ወይም የወንጭፍ ድንጋይ ይቀ
ለጥማትና ከጥቅም ውጪ ትሆናለች ።

ወርቅ ፡ የዓለም ሕዝብ የሚኖረው ፡ በመከባበርና በመደ
ጋገፍ መሆኑን ረስቶ «ከኔ በቀር ማን ሰው አለ»
እያለ የሚኩራራና የሚብለጠለጥ ሰው የሥራ ጓደ
ኞቹ ይጠሉታል፤ አለቃውም ራሱን ወዳድ መሆኑን

አይቶ ይንቀውና በብስጭት ላይ ወድቆ አጉልና ብቸኛ ሆኖ ይቀራል ።

ወርቅ ፡ ከሰፈሩ ጎብረተ - ሰብ ውጪ ሆኖ የሚኖር ሰው በአንድ ምክንያት የተነሣ ቀንም ሆነ ሌሊት ቢጮኽ ረዳት አያገኝም ። የሞትም አደጋ ቢደርስበት ፤ የዕድር ርዳታና ክብር ስለማይደረግ ለቱ ፤ በኃዘን ላይ ፡ ችግር ይደርስበትና በጣም ይበሳጫል ።

ለኻያጅ ፡ የለውም ወዳጅ ።

ሰም ፡ አገር ጥሎ ቁርበት ጠቅልሎ ለሚኼድ ፡ ወይም ለሚሰደድ ሰው ፡ ወዳጅ የለውም ፤ ምክንያቱም ከኼደበት ቦታ ተመልሶ የመገናኘትና የመጠቃቀም ተስፋ ስለማይጣልበት ነው ።

ወርቅ ፡ ከዚህ ዓለም ላይ በሞት ተለይቶ ላይመለስ ወደ መቃብር ቦታ ለሚወሰድ ሰው ፡ ወዳጅ የለውም ፤ ምክንያቱም ፡ ሌላው ይቅርና ፡ በሕይወቱ ሳለ ይወደውና ያከብረው የነበረው ዘመዱ እንኳን ሬሣውን ከገዛ ቤቱ በቶሎ አውጥቶ ፡ ቀብሮ ለማረፍ ስለሚቸኩል ነው ።

ወርቅ ፡ ከሹመቱ ለተሻረ ሰው ፡ ወዳጅ የለውም ፤ ምክን ያቱም እንግዲህ እንደገና ተመልሶ አይሾምብንም፤ ከማለታቸው የተነሣ ፡ ሌላው ይቅርና በሹመቱ ላይ ሳለ ፤ ይሚገቱለት የነበሩት ሰዎች እንኳ ነገ ርን እየፈጠሩ ፤ ስለሚከሱትና ፤ ስለሚፈርዱበት ነው ።

ጩኽት ለቁራ ፡ መብል ለአሞራ ።

ሰም ፡ በአንድ ከፍተኛ ነገር ላይ ወጥቶ እንደ ቃፊር የሚበሉትን አሞሮችን እየጠበቁ መጮኽ ብቻ ለቁራ የተመደበ ነው ፤ ጥንቡን ከቦ እንደልብ እየዘነጠሉ መብላቱ ግን ለአሞራ ብቻ የተሰጠ ነው ።

ወርቅ ፡ በደረቅ ወንበር ላይ ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብሎ ሥራን መሥራቱ ብቻ ለተራ ሠራተኛ የተመደበ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ብቅ እያሉ፤ ከተሠራው ጽሑፍ ውስጥ ሩቡን እየፈረሙ በምቾት መኖሩና በበላዮችም ዘንድ መመስገኑ ግን ለባለ ሥልጣኑ ብቻ የተሰጠ ነው ።

ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ፡ ይበጣጠስ ።

ሰም ፡ በጥምቀት የዓመት በዓል ቀን ተጠልቆ ያልታየ ቀሚስ ፡ (የማዕርግ ልብስ) እንዳለ ስለማይቈጠር ፤

ተጠልቆ ይለቅ ፡ ይበጣጠስ ፤ እንጂ ፤ የክት ሆኖ መዋል የለበትም ።

ወርቅ ፡ ለተቸገሩ ወገኖቹ የማይተርፍ ሀብታም ፡ ባለጸጋ ነው ፤ ሊባል አይገባውም ፤ ምክንያቱም ድሾች ዘመዶቹ ጦማቸውን ሲያድሩ ፤ እሱ ብቻ ተንቀባርሮ ሊኖር ፤ ስለማይገባና አኳኋኑም የተሟላ ስለማይ ሆን ነው ።

ወርቅ ፡ ለሀገሩ ክብር ፡ ለሕዝቡም ነፃነትና ኩራት የማ ይሞት ወታደር የገባበትን ግዴታ ባለመፈጸሙ ፡ በባልደረቦቹ እጅ ይገደል ፤ ምክንያቱም ጠላት እናት ሀገሩን ለመውረር እየገፋ ሲመጣ ፤ ሸሽቶ በማምለጥ ወይም ተደብቆ ራሱን ብቻ ከማዳን ይልቅ ፡ በጀግንነት እየተዋጋ ፡ ድል ማድረግ ፡ ወይም መሞት ስለሚገባው ነው ።

ላም ፡ ነጂዋን እንጂ ፤ ጌታዋን አታውቅም ።

ሰም ፡ ላም ፡ ምንደኛ ሆኖ እየነዳ የሚጠብቃትን እንጂ ፤ ገንዘቡን አውጥቶ የገዛትንና በጣም አድ ርጎ የሚያስብላትን ጌታዋን አታውቅም ።

ወርቅ ፡ ጠልቆ የማያስብ ፡ ወይም አያሌ መጻሕፍትን ያላነበበ ሰው ፡ ጊዜን አይቶ በሚወደውና በሚከ ዳው ባልንጀራው ላይ ፡ እምነቱን ይጥላል እንጂ ፤

በደስታና በመከራ ጊዜ የማይለየው ፡ ያው የሥጋ ዘመዱ ብቻ መሆኑን አረጋግጠ አያውቅም ።

ደጃቸውን ሳይዘጉ ፤ ሰውን ሌባ ይላሉ ።

ሰም ፡ ደጃቸውን አጥብቀው ሳይዘጉና በቁልፍም ሳይቁ ልፉ ፤ እየተዉ ኼደው ሲያበቁ ፤ የራበው ፡ ወይም የስርቆት ሱስ ያስገደደው ፡ ቢሞጨልፋቸው ፤ ሰውን ሌባ ይላሉ ።

ወርቅ ፡ የምሥጢር በር አፋቸውን በትዕግሥት መዝ ጊያ ሳይዘጉና ማንም ሳያስገድዳቸው ምሥጢራቸ ውን ራሳቸው ዘክዝከው ሲአበቁ ፤ ሰውን « አይ ቋጥሬ ውሸታም» እያሉ ያማሉ ፤ ይሰድቡም አል ።

ልብ ካዘነ ፤ ዕንባ አይገድም ።

ሰም ፡ ልብ በምር ካዘነና ከከፋው ዘንድ ፤ ዕንባን ከዓይን ውስጥ ጨምቆና አፍልቆ ለማፍሰስ ወይም ለማንባት ምንም አይቸግርም ።

ወርቅ ፡ ማንም ሰው በጎ ሥራን ለመሥራት ከልቡ ካሰ በበት ፤ በሚቻለው መጠን የተቸገረውን ለመር ዳት ፡ ያዘነውንም ለማስደሰት ከቶ አያቅተውም ።

የአህያ ባል ፡ ከሾተ አያስጥል ።

ሰም ፡ አለሌ ወይም ወንድ አህያ ፡ ምንም እንኳ የሴት አህያ ባል ቢሆንም ቅሉ ፤ ሚስቱን አህያን ከጠላቱ ከሾተ አፍ ለማስጣል ችሎታ የለውም ።

ወርቅ ፡ ድኻ ወይም መጥፎ አባት ምንም እንኳ የቤተ - ሰቡ ኃላፊ ቢሆንም ቅሉ ፤ ቤተ - ሰቡን ከችግርና ከድንቁርና ሊያድናቸው አይችልም ።

በሰው ቂጣ ፡ እጅህን አትቃጣ ።

ሰም ፡ ብርቱ ቅጣት ፡ ከሐፍረትና ከጸጸት ጋራ እንዳ ይደርስብህ ሌላ ሰው ፡ የደከመበትን ሀብት ለመ ስረቅ እጅህን ከቶ አትዘርጋ ።

ወርቅ ፡ በሥጋህ በኩል ምድራዊ ነቀፌታና ቅጣት ፡ በነፍስህም ረገድ ፡ ሰማያዊ ኵነኔ እንዳይፈረድ ብህ በባልና ሚስት መካከል ፍጹም አትግባ ። እንዲሁም እንደ እርጎ ዝንብ በሰው ነገር ጥልቅ አትበል ።

ኼዳ ጉበት ይነሷታል ፤ ታላቅ ታናሽ
ሰደዱልኝ አለች !

ሰም ፡ ራሷ ኼዳ ሥጋን ብትለምን ፤ ጉበትን እንኳ ሲነሷት ፤ እቤትዋ ቁጭ ብላ ታላቅ ታናሽ ሥጋን ለመላክተኛ ሰደዱልኝ ፤ አለች ።

ወርቅ ፡ ጠንቋይ በራሱ ላይ የሚደርስበትን ነገር ሁሉ ፡ ለራሱ እንኳ ምንም የማያውቅ ሲሆን ፤ የዋሆቹን ሰዎች የሕይወትንም ሆነ የሞትን ፡ የሀብትንም ሆነ የሹመትን ዕድል አውቅላችኋለኹ ፤ እያለ ያታልላቸዋል ።

ሆድን በጐመን ቢደልሉት ፤ ጉልበት ፡ በዳገት
ይለግማል ።

ሰም ፡ ሆድን በጐመን ምግብ ብቻ ወስነው ቢሞ ሉት ፤ ወይም ቢያጠግቡት ፤ ጉልበት ድክምክም እያለው ዳገትን መውጣት ይሳነዋል ።

ወርቅ ፡ አሠሪዎች ሠራተኛን በጥቂት ደመወዝ ብቻ ወስነውና ጨቁነው ቢያሠሩት ፤ የመሥራት ፍላጎቱ በቀቢጸ ተስፋ ይደክምና ሥራው በጣም ይበደላል ።

ለአህያ ማር አይጥማትም ።

ሰም ፡ ለአህያ ኮሸሸላ ፡ ወይም የጠላ አተላና አሠር እንጂ ፤ ጣፋጩ ማር አይጥማትም ።

ወርቅ ፡ ለተረገመ ሰው ድንቁርና እንጂ ፤ ትምህርት ፡ ቅጣት እንጂ ፤ ምክር ፡ ጥል እንጂ ፤ ፍቅር ፡ ከቶ አይስማማውም ።

ከታጠቡ ፤ እስተክንድ ፤ ከተጫወቱ ፤ እስተሆድ ።

ሰም ፡ ጣትን ከታጠቡ ዘንድ ፤ እስተ ክንድ ድረስ ሙልጭ አድርጎ መታጠብ ይገባል ፤ ምክንያቱም ጣቶች ብቻ ታጥበው ክንድ ቢቀር ፤ የተሟላ እጥ በት ስለማይሆን ነው ። እንደዚሁም መጫወት ፡ ወይም መወያየት ካልቀረ ፤ ከመተፋፈርና ከመፈ ራራት የተነሣ ከአንገት በላይ ሳይሆን እውነቱን ግልጽ አድርጎ ከአንጀት መጫወት ይገባል ፤ ይህ ባይሆን ግን በተጫዋቾቹ መካከል መተማመን ሊገኝ አይችልም ።

ወርቅ ፡ ትምህርትን ከተማሩ ዘንድ ፤ እስተ መጨረ ሻው ድረስ ጠንክሮ መማር ይገባል ፤ አለበ ለዚያ ግን ከተማሩት ጓደኞች ጋራ እኩል ሆኖ ለመኖር አይቻልም ። እንደዚሁም ከተጋቡ አይ ቀር ፤ ልጆችን መውለድ ይገባል ፤ ካልሆነ ግን በባልና ሚስት መካከል ከልብ የሆነ መተማመን ፡ መፋቀርና መተዛዘን መኖራቸው ያጠራጥራል ።

ሲያገሮሱት የማያገሮስ ፡ ከቀማኛ ይቈጠራል ።

ሰም ፡ ከአፉ ጋር የሚመጣጠነውን ጥሩ ጉርሻ እያበጁ በጥንቃቄ ሲያገሮሱት ፤ እጁን የተሠበረ ሰው ካልሆነ በስተቀር ፤ እርሱም በተራው መልሶ የማያገሮስ ፡ ከቀማኛ ይቈጠራል ።

ወርቅ ፡ ተቀጥረው ለሥራ በየተላኩበት መሥሪያ ቤት እየተገኙ ፤ የሚፈለግባቸውን ሥራ በቅንነትና በት ጋት ሲሠሩለትና ሲያገለግሉት ፤ የከሠረ መሥሪያ ቤት ካልሆነ በስተቀር ፤ እርሱም በበኩሉ ፡ ሠራ ተኞቹን በበቂ ደመወዝና በየዓመቱ ጭማሪ የማ ያስደስተው አሠሪ ፤ ከቅኝ ገዢዎች ይቈጠራል ።

ገንዘብ ካለ ፤ በሰማይ መንገድ አለ ።

ሰም ፡ ገንዘብ ካለ ዘንድ ፤ በአይሮፕላን ተሳፍሮ በሰማይ ላይ እየበረሩ ፤ ለመጓዝና በጥቂት ሰዓ ቶችም ወደፈለጉበት አገር ለመድረስ ይቻላል ።

ወርቅ ፡ ገንዘብ ካለ ዘንድ ፤ በገንዘቡም የተራቡትን ካበሉበት ፤ የተጠሙትን ካጠጡበት ፤ የታሠሩትን ካስፈቱበት ፤ የታመሙትን ካሳከሙበት ፤ በሰ ማይ ቤት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስና የእግዚአብሔርን ክብር ለመቀደስ ይቻላል ።

ወርቅ ፡ ትልቅ ወገን ካለ ፤ ወይም ብዙ አጋር ከተ ገኘ ፤ በማንኛውም ቦታ ላይ ሥራም ሆነ ሕክ ምና ሹመትም ሆነ የደመወዝ ጭማሪ ያለድካ ምና ያለበቂ ትምህርት ለማግኘት ይቻላል ።

ወርቅ ፡ ኧላ ከባድ ድክነት ተጭኖህ የተወለድክበትን ቀን ላለመርገም ብትፈልግ ፤ በጐልማሳነትህ ጊዜና ወደፊትም በእርጅናህ ሰዓት ትደሰትበትና ትንቀባረርበት ዘንድ ፡ አሁን ገንዘብ ሳለህ ገንዘብ ህን ጠቃሚ በሆኑ ሥራዎች ላይ አውለው።እንደዚ ሁም ደግሞ ካደግህ በኧላ ፤ የምትማርበትን ጊዜ አጥተህ በጸጸት አለንጋ እንዳትገረፍ ከፈለግህ ፤ አሁን አንተጋ የልጅነት ዕድሜ ሳለ ጥበብን ለመቅሠም ወደ ትምህርት ቤት ቶሎ ቶሎ ሩጥ ።

የእህል ጌታ ፈርዛዛ ፤ የወርቅ ጌታ ቀበዝባዛ ።

ሰም ፡ ፈጥኖ ባይሸጥም እንኳ ፤ ከያዘው ቀንሶ በልቶ ስለሚያድር ፤ ባለ እህል ፡ በገበያ ላይ ምን ጊዜም ቢሆን ኩሩ ነው ፤ ሽምቶ በላ ግን ቀበዝባዛ ነው ፤ ምክንያቱም የያዘው ወርቅ ፡ ወይም ብር አይቂ ረጠም ነገር ከመሆኑ የተነሣ ፡ ጠሙን እንዳያድር ስለሚፈራ ነው ።

ወርቅ ፡ በሐሰት ተወንጅሎ በሕግ ፊት ቢቀርብም እንኳ ፤ ከወንጀሉ ንጹሕ መሆኑን ከማወቁ የተ ነሣ ፡ እውነትን የያዘ ሰው ምን ጊዜም ቢሆን ልቡ ደንዳና ነው ፤ ተከስሶ በሐሰት የሚከራከር ሰው ግን ልበ ድንጉጥ ፊቱ ልውጥ ነው ፤ ምክንያቱም

ካልጠገቡ አይዘሉ ፤ ካልዘለሉ አይሠበሩ ።

ሰም ፡ በጥጋብ ስሜት በጣም ካልተገፋፉ በስተቀር ፤ ያለ ጥንቃቄ መዝለል ፡ የለም ። ካልዘለሉም ፤ የመውደቅና የመሠበር አደጋ በራስ ላይ ፈጽሞ አይደርስም ።

ወርቅ ፡ ምን ይመጣብኛል ፡- በሚል በማያዋጣ መጥፎ አሳብ ካልተገፋፉ በቀር ፤ ሕግን ለመተላለፍ ከቶ አይቃጣም ። በዚሁ አኳኋን ሕግን ካልተላለፉም ፤ የመታሠር ፡ ወይም የገንዘብ ፡ ወይንም የሞት ቅጣት በራስ ላይ ፈጽሞ አይደርስም ።

አባት ሳለ አጊጥ ፤ ጀምበር ሳለች ሩጥ ።

ሰም ፡ በኧላ የቤተ ሰብ ኃላፊ ሆነህ ይበልጡኑ ለቤተ ሰብ ብቻ የማሰብና ለራስም የመንፈግ ዝንባሌ የመጣ ጊዜ ፤ እንዳይቈጭህ ፡ አባት ፡ በሕይወት ሳለ ፤ በአ ባት አሳቢነትና አሳዳሪነት አሁን ብቻ አጊጥ ፤ ተደሰት ፤ ተንቀባረር ። እንደዚሁም ኧላ ጥቅጥቅ ያለ ጭለማ መጥቶ መንገዱ እየተሳሳተ ፤ ዕንቅፋቱ የእግሮችህን ጣቶች እያነጐደ ፤ እሾሁ እየወጋ ፤ ቁጥቋጦው ቀማኛን ወይም አውሬን መስሎ እየ ታየህ ስትጨነቅ እንዳይቈጭህ ፡ ጀምበር ሳለች ፤ አሰብክበት ቦታ ለመድረስ ቶሎ ቶሎ ሩጥ ።

ወርቅ ፡ ማንኛውም ዓይነት ችግር ቢያጋጥመውም ፤ የሚያስፈልገውን ርዳታ ካንዱ ዘንድ ቢያጣ ፤ ካንዱ ስለሚያገኝ ፤ ትልቅ ወገንና ብዙ አጋር ያለው ሰው ጥቃት ፡ ወይም መጉላላት አይደርስበትም ።

ወርቅ ፡ ልዩ ልዩ ሞያና የእጅ ጥበብ ያለው ሰው ባንዱ ሞያው ባይፈለግ ፤ በቀረው ጥበቡ ተቀጥሮ እየሠራ በደስታና በምኞት ስለሚኖር ፤ ብስጭት ወይም ችግር አያገኘውም ።

የመንታ እናት ፡ ተንጋልላ ትሞት ።

ሰም ፡ የመንታ ልጆች እናት መንታዎቹን ልጆችዋን ከቀኝና ከግራ ጐኗ አድርጋ ለማጥባት ስትል ተንጋልላ ትሞታለች ።

ወርቅ ፡ እርስ በርሳቸው የማይስማሙና የማይጣጣሙ ዘመዶች ያሉት አስተዋይ ሰው ፡ ሁለቱንም ወገኖች እንደየጠባያቸው ሲቀበልና ለማስማማትም ሲሞክር ከያንዳንዳቸው በሚደርስበት ኩርፊያና ጉርምርምታ ሲከፋውና ሲሠቃይ ይኖራል ።

የሸቦ ችኩል ፡ ቀንድ ይነክሳል ።

ሰም ፡ የሸቦ ችኩል ከብቶችን ሲያይ ፤ የሚይዘውንና የማይዘውን ብልት ስለማያውቅ ፤ ምንም ሥጋ የሌለበትን የእንስሳን ቀንድ ተርበትብቶ ይነክሳል ።

አፈ ጮሌ ፤ ወይም ብልጥ ቢሆንም ቅሉ ፤ የሠራውን ሥራ ከልቡ ውስጥ የማይዘነጋው በመሆኑ ብቻ ነው ።

ከተማረ ፡ የተመራመረ ።

ሰም ፡ በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ ባገኘውና በገበየው ትምህርት ብቻ ተወስኖ ከሚኖር ከተማረ ሰው ይልቅ ፡ በዕውቀትና በመራቀቅ ለመደርጀት ፡ ዘወትር መጻሕፍትን እያነበበ ፡ ራሱም እያሰበና እየተፈላሰፈ የተመራመረ ሰው ይበልጣል ።

ወርቅ ፡ ሀብትን በውርስ ካገኘ ሰው ይልቅ ፡ ራሱ ጥሮ ግሮ የበለጸገ ሰው ይበልጣል ፤ ምክንያቱም ሀብቱን በውርስ ያገኘ ሰው በገንዘቡ ስላልደከመበት ፤ ሀብቱን በመጠጥና በሴሰኝነት ፡ በጨዋታና በዙረት ላይ አውሎ ራሱን ለድኽነትና ለበሽታ አሳልፎ የሚሰጥ ሲሆን ፤ በራሱ ልፋትና ጥረት የበለጸገው ግን ገንዘቡን በጥንቃቄ ይዞ በሚገባ ሥራ ላይ እያዋለ ስለሚጠቀምበት ነው ።

፪ ጉድጓድ ያላት አይጥ ፡ አትሞትም ።

ሰም ፡ ጠላት ለመግደል ሲመጣባት ካንዱ ወደ አንዱ እየተዘዋወረች ስለምታመልጥ ፪ ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም ።

ወርቅ ፡ ችኩል የኾነና መላ የለሽ ሰው ፡ ተግባሩን በማስተዋል ስለማይፈጽም ብዙ ጊዜ አስቦ ፡ አንድ ጊዜ ብቻ የሚሠራውን ሥራ ፡ እየሠራና እያፈረሰ ዐሥሬ ይሠራዋል ።

ወርቅ ፡ የሰው ችኩል ፡ በጨረፍታ የሰማውን ነገር እስቲአረጋግጥ ድረስ ፤ ሌላ የሚቀድመው ስለ ሚመስለው የወሬን ጫፍ ብቻ ይዞ ፡ የታመመ ውን ሞት ፤ ብሎ ሲኦረዳ የወደቀውንም ደግሞ ተሰበረ ብሎ ያወራል ።

እርጥብ ሬሣ ፡ ደረቁን አስነሣ ።

ሰም ፡ ትኩስ ፡ ወይም ዕድለኛ ሬሣ ፡ የሕይወት ነፍስ ከተለየችው የቆየውንና የደረቀውን ሬሣ ሲነ ካው በተአምር ነፍስ ዘርቶ እንዲነሣ አደረገ ።

ወርቅ ፡ የአንድ ነገር አዲስ መሻሻል ፡ በሰበቡ ሌላ ሊሻሻል የሚገባውንና የተረሳውን ነገር ፡ ከሱ ቀጥሎ እንዲሻሻል አስታወሰ ።

ወርቅ ፡ አዲስ አምባ ዓሮ ፡ የቄየውንና ወደ መረሳ ትም ያዘነበለውን የዱሮ ቂም በሰበቡ እንደገና አድሶና አባብሶ በማስታወስ ቀሰቀሰ ።

የረጋ ወተት ፡ ቅቤ ይወጣዋል ።

ሰም ፡ በአንድ ዕቃ ውስጥ ቆይቶ የረጋ ወተት ሲናጥ ፤ ማንኛውንም ነገር የሚያርስና በሌላውም በኩል በጣም ጠቃሚ የሆነው ቅቤ የሚባለው መድኃኒት ይወጣዋል ።

ወርቅ ፡ ማንኛውንም ነገር በትዕግሥት የተቀበለና በተስፋም የጠበቀ ሰው የድካሙን ፍሬ ያገ ኛል ። የተመኘውንም ሁሉ ለማየት ይበቃል ።

የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው ፡- በሻሽ ። የኋለኛው እንዳይሸሽ ።

ሰም ፡ የፊት ወዳጅህን በምን ገንዘህ ቀበርከው ፡- በነጭ ሻሽ ። ስለምን ፡- የኋለኛው ወዳጄ ውለታ ቢስ ነው ፤ ብሎ እንዳይሸሽብኝ በማሰብና በመፍራት ነው ።

ወርቅ ፡ የመጀመሪያው ወዳጅህን በምን አስደሰትከው ? በታማኝነት ፤ በጨዋነትና ፡ በረዳትነት ፤ ባጭ ሩም ለኔ ሊያደርጉልኝ የምፈልገውን ሁሉ ለሱም በማድረግ ነው ፤ ስለምን ፡- በዚህ ዓለም ላይ ያለ ጎብረተ-ሰብ ለመኖር ስለማይቻል ፤ የቀረውም ወዳጄ እንዳይርቅብኝ ብዬ ነው ።

ከማቃጠል ተግባሩ ቢታገሥ ፤ ገለባ ሲቀብጥ መጥቶ ጐበኘውና ተቃጥሎ ዐረፈ ።

ወርቅ ፡ ልማደኛው የመጀመሪያውን ወንጀል ፈጽሞ ሳይጋልጥ ቢቀር ፤ በሠራው መጥፎ ሥራ በመጸጸት ፈንታ እንደ ተዚህ ቀደሙ አመልጣለሁ ብሎ ፡ ሌላ ወንጀል ሲሠራ ተያዘና ፡ በሚገባ ቅጣቱን ተቀበለ ።

ራት የሌለው ቄስ ፡ እንደ ልቡ አይቀድስ ።

ሰም ፡ በቂ የመተዳደሪያ ሀብት የሌለው ቄስ ፡ እኔና ቤተ ሰቦቼ ምን እንበላለን ፡- ምንስ እንለብሳለን ፡- በማለት ስለሚጨነቅ ፤ እንደ ልቡ አይቀድስም ። እንደ ልቡ ሆኖም አይሰብክም ፤ ለሚገባቸውም ምሥጢረ ጥምቀትንና ምሥጢረ ቁርባንን አይሰጥም ።

ወርቅ ፡ ሙሉ ጤና የሌለው ሰው ያገኘውን ፡ ወይም የተገኘውን እንደ ልቡ ሊመገብና ከሰዎችም ጋራ ሊጫወት ፡ እንደ ሰውም ሁሉ ሥራ ሠርቶ ፡ ደመወዙን አግኝቶ፤ያለበትን ችግር ሊያቃልል አይችልም።

ወርቅ ፡ በቂ ትምህርት ወይም የብዙ ጊዜ የሥራ ልምምድ የሌለው ሰው ፡ የተሰጠውን ሥራ በደንብ ሊፈጽምና የቀረበለትም ጥያቄ በየመሥመሩ ሊመልስ አይችልም ።

ፀጉራም ውሻ ፡ አለ ሲሉት ፤ ይሞታል ።

ሰም ፡ ፀጉራም ውሻ የፀጉሩ ብዛትና ርዝመት ፡ ክሳቱን ፤ ወይም የገላውን ጉዳት ስለሚሸፍነው ፤ ደኅና ነው ፤ ሲሉት ፤ ውስጥ ውስጡን ያልቅና ድንገት ይሞታል ።

ወርቅ ፡ ብዙ ዓይነት ልብሶችን እያቀያየረ በመልበስ ገንዘብ ያለውና የተረፈው መስሎ ውጪ ውጪውን የሚታይ አንዳንድ ሰው ፡ ውስጡን ሲአዩት ፤ ምንም የሌለው ባዶ ኾኖ ይገኛል ።

የለመደች ጦጣ ፡ ኹል ጊዜ ሽምጠጣ ።

ሰም ፡ ሰውን እያዘነጋች ማንኛውንም ነገር ነጥቃ ማምለጥን የለመደች ጦጣ አመልጣለሁ ማለትን እንጂ፤ እያዛለሁ ማለትን ስለማታውቅ ፤ ሁል ጊዜ የሰውን አዝመራ መሸምጠጥዋን አትተውም ።

ወርቅ ፡ ሲመቸው፤ ማንኛውንም መጥፎ ነገር እየፈጸመ ማስተባበልን የለመደ ሰው ፡ አይገለጽብኝም ማለትን እንጂ ፤ ያጋልጠኛል ማለትን ስለማያውቅ ፤ ያንኑ የለመደውን አመል ከማድረግ አይመለስም።

እሳት ቢአንቀላፋ ፤ ገለባ ጐበኘው ።

ሰም ፡ እሳት ቢአንቀላፋ ፤ ማለት ቢዳፈን ፤ ወይም

ያሳደኩት ውሻ ፥ ነከሰኝ ። ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ ።

ሰም ፥ ከቡችላነቱ ጀምሮ ያሳደኩት ውሻ ያለመጠን ከመጥገቡ የተነሣ አሳዳጊውና ጌታው መሆኔን ረስቶ ነከሰኝ ። እንዲሁም እንዳይጠፋ ስል እፍ ! እፍ ! እያልኩ በስንት ልፋት ያነደድኩት እሳት መልሶ እኔን ጠበሰኝ ። (ፈጀኝ)

ወርቅ ፥ ተርቦ ያበላሁት ፥ ታርዞ ያለበስኩት ፥ ሥራ አጥቶ ያስቀጠርኩት ሰው ፥ በመልካም ውለታ ፈንታ ክፉ ዋለብኝ ። በመውደድ ፈንታ ጠላኝ ። እንዲሁም በጣም ተቸግሮ ሳለ ገንዘቤን በእ ምነት ያበደርኩት ሰው ብድሩን ከምስጋና ጋር በመመለስ ፈንታ አላውቅም ብሎ ካደኝ ። ከነአካቴውም እንደ መቅረብ ፈጽሞ ሸሸኝ ።

ቀጥኜ ቢያየኝ ፤ ጅማት ለመነኝ ።

ሰም ፥ ከጉዳት የተነሣ በጣም ቀጥኜና ከስቼ ሥሬም ሁሉ ተገታትሮ ቢያየኝ ፤ በሕይወት እያለሁ የራሴን ወይም የገላዬን ጅማት ለመነኝ !

ወርቅ ፥ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ፍጹም ድኻና ብዙ ዘመድ አልባ መሆኔን ቢያየኝ ፤ ምንም አያደርገኝ ብሎ ናቀኝና በጣም አጠቃኝ !

ዕውር ዕውርን ቢከተል ፤ ተያይዞ ገደል ።

ሰም ፥ ዕውር ይመራኛል ብሎ ዕውርን ቢከተል ፤ ተያይ ዘው ወደ ገደል ይገባሉ እንጂ ፤ መሪው ዕውር ተመሪውን ዕውር በደኅና እየመራ አሰበበት ቦታ ከቶ አያደርሰውም ።

ወርቅ ፥ መሃይምናን ያልተማረውንና እውነተኛ ያል ሆነውን ቄስ የንስሐ አባት ቢያደርጉ ፤ ቄሱና የንስሐ ልጆቹ ሁሉም አብረው ገሃነመ-እሳት ይገ ባሉ እንጂ ፤ ቄሱ መሃይምናኑን መክሮና አስተምሮ መንግሥተ-ሰማያትን አያስወርሳቸውም ።

ፅንቅልፍ ታበዛ ፤ ከነብር ትፋዘገር ።

ሰም ፥ ከነብር ጋራ ትፋጠጪአለሽ ፤ ነገር ግን እን ቅልፍን ታበዢአለሽ ፤ ታዲያ ለመመከትም ሆነ ለማምለጥ እንዴት ይቻላል ።

ወርቅ ፥ ከትምህርት ጋራ የምታገል ተማሪ ነኝ ትያለሽ ፤ ዳሩ ግን ተሸቀርቅረሽ ከመዞር በስተቀር ጥናት የሚሉትን በዓይኔ አታሳዩኝ ትያለሽ ፥ ታዲያ ትምህርትን ተምሮ ለመጨረስም ሆነ ፈተናን በሚገባ ለማለፍ እንዴት ይቻላል ፦

የማይደርሱበትን አያኩም ።

ሰም ፥ በሰው ፥ ወይም በሌላ መሣሪያ ካልሆነ በስተ

በኼደበት ቦታ የሚገኘው ዳዋ ተደበደበ ፤ ተጨ
ፈጨፈ ፡ ተቃጠለ ማለት ነው ።

ወርቅ ፡ አንዱ ባጠፋ ፤ ወይም ያጠፋ ሰው እያለ ፤ በማ
ወቅ ፡ ወይም ባለማወቅ ግርምቢጥ ያላጠፋ ሰው
ተቀጣ ማለት ነው ።

ሌባ ላመሉ ፡ ዳቦ ይልሳል ።

ሰም ፡ የሰውን ዳቦ እንዳይሰርቀው አልተመቸውም ፤
እዚያው ሳለ እየተገላመጠ እንዳይበላው ጠግ
ቦአል ፤ ነገር ግን ሌባ ላመሉ ወይም ልማዱ
እንዳይታገል ሲል ዳቦን ይልሳል ።

ወርቅ ፡ ውሸታም ሰው የመዋሸት ልማዱ እንዳይታ
ገል በመገደዱ ብቻ ከልብ የሚወደውንና
በብዙ የሚጠቅመውን ፅኑ ወዳጁን አሳብቆ
ከሰው ጋር ያጣላዋል ።

ዓሣን መብላት ፡ በብልሃት ።

ሰም ፡ ዓሣን መብላት በብልሃትና በትዕግሥት ነው ፤
አለበለዚያ ግን ያሉ የማይመስሉ ቀጫጭንና
የጉብስ ምርቅ የሚያክሉ አጥንት ስላሉበት ፤
ከፍ ብሎ በጉሮሮ ውስጥ ዝቅ ብሎ በጨጓራ
የተሰኩ እንደሆን አደጋን ያስከትላሉ ።

ቀር የማይደርሱበትን የገላ ክፍል ቢያሳክክም
እንኳ ፤ በራስ እጅ ለማከክ አይቻልም ።

ወርቅ ፡ ሲያዩት ምንም እንኳ እጅግ ቢያምርም ቅሉ ፤
ላይገኝ ከዓቅም በላይ የሆነውን ነገር ሁሉ
አጥብቆ መመኘት ከንቱ ድካምና መማቀቅ ነው።

ወርቅ ፡ እንደ ሠራው ሊሠሩበት ፡ ወይም ሊቋቋሙት
የማይቻል ኃይለኛ ጠላት ስለ ወዳጅ ይቁጠ
ራል ፤ ምክንያቱም ላይጠቅም ቢነካኩት ፤ ትርፉ
በገዛ እጅ ራስን ማጥፋት ስለሆነ ነው ።

ለራስ ሲቈርሱ ፤ አያሳንሱ ።

ሰም ፡ ማንም ሰው እንጀራንም ሆነ ዳቦን ለራሱ ሲቆርስ
የቁራሹን መጠን ከቀሩት በለጥ አድርጎ ይቆር
ሳል እንጂ ፤ ምንም ቢሆን ፈንታውን አያሳንስም ።

ወርቅ ፡ ማንም ሰው በዕውቀትም ኾነ በጉልበት ፡ በዘ
ርም ሆነ በሀብት ስለ ራሱ ሲናገር ንግግሩን
በጣም እያጋነነ ከፍ ከፍ ያደርጋል እንጂ ፤ ምንም
ቢሆን ዝቅዝቅ እያደረገ ሲናገር አይሰማም ።

አይጥ በበላ ፤ ዳዋ ተመታ ።

ሰም ፡ አይጥ ዳቦውን ፡ ወይም እኽሉን ቅርጥፍ አድ
ርጎ በበላ ፤ ዳዋ በዱላ ተመታ ፤ ማለት በአይጡ
ላይ ዱላውን ሲሠነዝሩበት አይጡ አምልጦ

ወርቅ ፡ ገንዘብን መያዝ በጥንቃቄ መኾን አለበት ፤ አለበለዚያም ወደፊት ይከፈላል ፤ እስከዚያውም ማንም ሊያውቀው አይችልም የሚያሰኝ አታላይ ሐሳብ ስለሚያስመጣ ፤ የግል ሀብት ቢሆን መደኽየትን ፤ የመንግሥት ገንዘብ ቢሆን ከሥራ መውጣትንና ውርደትን መታሠርንና መወረስን ያስከትላል ።

ከአያያዝ ይቀደዳል ፤ ከአነጋገር ይፈረዳል ።

ሰም ፡ አያያዝን ካለማስተካከል የተነሣ አንድ ነገር ባል ተፈለገው ቦታ ላይ ይቀደዳል ። እንዲሁም ምንም እንኳ በእውነት ተነሥቶ ቢሟገቱም ቅሉ ፤ አነጋገርን ወይም የነገርን አቀራረብ ካለማወቅ የተነሣ በፍርድ ቤት ይፈረዳል ፡ ማለት ያስረታል ።

ወርቅ ፡ የባልን አያያዝ ካለመማርና ካለማወቅ የተነሣ ፡ ባል ሚስቱን እያዘነ ይከዳል ። እንዲሁም ዓቅምንና ልክን ያለ ማወቅ ከመጉዳቱም በላይ ያስነቅፋል ።

ተናካሽ ውሻ ፡ የኾብ መቋደሻ ።

ሰም ፡ ተናካሽና አጥባቂ ውሻ ፡ የሚያስጥሉት ሰዎች ወይም የሚረዱት ውሾች ካሉበት ቦታ ተለይቶ ፡

ኾቡን እየተከተለና እያሳደደ ለመናከስ ስለሚኼድ ፤ የኾቡን የመጀመሪያ ጉርሻና የአፉም ማሟሻ ይሆናል ።

ወርቅ ፡ ጠብ አጫሪ ፡ ተሳዳቢና ተንኳሽ ሰው ቢታገሡ ፤ ትዕግሥትን የሚያስጨርስ ፡ ቢሸሹ የሚከተል በመሆኑ ምክንያት አነስ ቢል የመደብደቡ ፡ ላቅ ቢል የመገደሉ ገፈታ ቀማሽ ይሆናል ።

የሚፈታ ከተማ ፡ ነጋሪት ቢመቱ አይሰማ ።

ሰም ፡ የሚፈታ ፡ ወይም ጥፋ ያለው ከተማ ንስሐ በመግባት ፈንታ ፡ የኃጢአት ተግባሩን ይቀጥላል እንጂ ፡ በየአደባባዩና በየገበያው «ስማ ! ስማ ! ከሰይጣን ወደ እግዚአብሔር ካልተመለስክ ፤ ሰይፍ ይመዘዝብኻል ! » እያሉ ነጋሪት ቢመቱ ፤ በፍጹም አይሰማም ።

ወርቅ ፡ ከመሞት የማይተርፍ በሽተኛ ፡ እየተሻለው በመኼድ ፈንታ እየባሰበትና እየደከመ ይኼዳል እንጂ ፤ መርፌ ቢወጉት ፤ ክኒን ቢያቅሙት ምንም አይጠቅመውም ።

ወርቅ ፡ እንደ ሌላው አገር ሊሠለጥን የማይፈልግ ሕዝብ ፡ ዘመናዊውን ሥልጣኔ በመክተል ፈንታ ፡

የዱሮውን መጥፎ ልማዱን ይቀጥላል እንጂ ፤ ትምህርት ቤት ቢከፍቱ ፤ በጋዜጣና በራዲዮ ቢለ ፈልፉ ፤ የዝሆንን ጆሮ ይስጠኝ ፤ ይላል ።

የያዘውን ከወረወረ ፤ ፈሪ አይባልም ።

ሰም ፡ ወታደር ወይም ማንም ሰው ጠላትን ለመከላከል ሲል ፤ የያዘውን ጦር ከወረወረ ዘንድ ፤ ፈሪ ነው ሊባል አይገባውም ።

ወርቅ ፡ ማንም ሰው ወገኑን ለመርዳት በጠቅላላም ችግር ካገሩ ላይ ለማጥፋት ሲል ፤ የሚቻለውን ያህል ከለገሠ ዘንድ ፤ ንፉግ ነው አይባልም ።

የማሽላ ዘር ፡ ከነአገዳው ቸር ።

ሰም ፡ የማሽላ ዘር ፍሬው በእንጀራነት ፡ በአነባበሮነት በቂጣነት ፡ በገንፎነት ፡ በቆሎነትና በንፍሮነት እንዲሁም በጠላነት ፡ ለሰው ልጅ አገልግሎቱን ሲሰጥ ፤ አገዳውም ደግሞ የስኳርነት ጠባይ ስላለው ፤ በጥንቅሽነት ይበላል ።

ወርቅ ፡ በጨዋነታቸውና በደግነታቸው የታወቁ ባልና ሚስት ቤታቸው የስነ ሥርዓትና የመልካም አስተ

ዳደግ ትምህርት ቤት ይሆናል ። ልጆቻቸውም የነርሱን ምሳሌነት ስለሚከተሉ ፤ ለጋብቻ የሚመረጡ ፤ ለክህነትና ለሹመት የሚመደቡ ይሆናሉ ።

ውሻ ፡ በቀደደው ፤ ሹብ ፡ ይገባል ።

ሰም ፡ ውሻ እየሾለከ ካንዱ ወዳንዱ ቤት ለመዞር ሲል በቀደደው አጥር በኩል ሹብ የቤት እንስሳን ለመንጠቅ ሲል ፤ ሌሊት መጥቶ ከውጪ ወደ ግቢ ይገባበታል ።

ወርቅ ፡ አንድ ሕገ ወጥ ሰው ሕግን ፡ ወይም ሥነ ሥርዓትን ከሻረው ዘንድ ፤ ሌላ ወንጀለኛ ደግሞ የሱን መጥፎ አርአያ መከተሉ የማይቀር ነው ።

መሳሳል ፡ የጋራ ነው ።

ሰም ፡ የቢላዎች እርስ በርስ መሳሳል ፡ ወይም መፋጨት የጋሪዮሽ ስለታምነትን ያስገኛል እንጂ ፤ አንዱን ቢላዎ ብቻ የሚያተባ አይደለም ።

ወርቅ ፡ አሠሪና ሠሪ ፡ ገዢና ፡ ተገዢ ፡ ባልና ሚስት ፡ ሻጭና ገብዩ ፡ መሆን ጥቅሙ የጋራ ነው እንጂ ፤ የአንዱ ወገን ብቻ አይደለም ።

አደባባይ አይወድም አባይ ።

ሰም ፡ አባይ ጠንቋይ ፡ ሥራው የዋሆችን ማታለል በመሆኑ ምክንያት ፡ ብዙ ሰው ወደ ሚውልበት ወደ አደባባይ መኼድንና በግልጽ ቦታ መኖርን አይወድም ።

ወርቅ ፡ ሰባቂ ወይም ቀጣፊ ሰው እውነተኛው ነገር ፡ ተድበስብሶና ተለባብሶ እንዲቀር ነው እንጂ ፤ ፊት ለፊት መናገርንና የእውነትን መገለጽ አይ ወድም ።

አትብዱ ያላት ወፍ ፡ በጥቅምት ዓይኗ ይጠፋል ።

ሰም ፡ አትብዱ ያላት ወፍ ፡ የክረምቱን ወራት ዓይናማ በመሆን በችግር አልፋው ስታበቃ ፤ ለአዕዋፍም ሆነ ለሰው ልዩ ልዩ ምግብ እንደ ልብ በሚገኝበት በጥቅምት ወር ብስል ተጥሬ እያማረጠች በልታ እንዳትጠግብ ዓይኗ ይጠፋል ።

ወርቅ ፡ ያልታደለ ሰው ፡ አድጎ አእምሮው ከበሰለ በኋላ ፤ መፈጠሩን እስቲጠላ ድረስ ፤ በጣም ለመጸጸት

ትምህርትን በሚቀበልበት በልጅነት ጊዜው ወላጆቹንና አስተማሪዎቹን አሰልችቶ ቁማርተኛና ደረጃ አዳሪ ይሆናል ።

ዕንጨት ፡ ካልነሱት ፤ አይጠፋም እሳት ።

ሰም ፡ እሳት ዕንጨትን ወይም ማገዶን ካልነሱትና እን ዳይጨስም ከመቆስቆስ ችላ ካላሉት በስተቀር ፤ ግር ብሎ ነድዶ የበረደውን ያሞቃል ፤ ምግ ብን ያበስላል እንጂ ፤ ያለምንም ምክንያት ከቶ እልም ብሎ አይጠፋም ።

ወርቅ ፡ አንድ ሠራተኛ በቂ ደመወዙን በሚገባ ከከፈ ሉትና በተስፋ እንዲበረታም «አይዞህ ! አይዞህ ! » ካሉት ዘንድ ፤ አሠሪውን ለማስደሰት በቅንነትና በትጋት እየሠራ ያገለግላል እንጂ ፤ ያላንዳች ምክንያት ከቶ በሥራው አይለግምም ።

እባብን ግደል ፤ ከነበትሩ ገደል ።

ሰም ፡ እባብን ፡ ራስ ራሱን ቀጥቅጥና ግደለው ። ሬሣ ውም ደግሞ ተላላፊውን እንዳያስደነግጥና ፤ ምና ልባትም በትርህን ያቄሸሸው ደሙ ፡ እጅህን ነክ

ቶት ኖሮ ፤ እጅህም አፍህን በዝንጋዔ ቢነካው ፤ እንዳትመረዝ ፡ ከገደልክበት በትር ጋራ ፡ እባቡን ወደ ገደል ወርውረው ።

ወርቅ ፡ ከክፉና ከተንኮለኛ ሰው አጠገብ ራቅ ። ጥርጣሬ ህንም በሚያደርግልህ የማታለል ርዳታ እያስ ወገደ ፡ አንተን አዘንግቶ በክፉ ሥራው እንዳ ያጠፋህ ፡ ማንኛውንም ስጦታ ከሱ ዘንድ አት ቀበል ።

ዝም ባለ አፍ ፡ ዝንብ ፡ አይገባም ።

ሰም ፡ አፍ ፡ ካልተከፈተ በቀር ፤ አፍን ተጠግቶ ሲበር ሳለ ፤ ትንፋሽ ስለማይጠልፈው ፤ በከንፈሮች መዝጊያነት ክድን ባለ አፍ ውስጥ ዝንብ አይ ገባም ።

ወርቅ ፡ ምንም እንኳ በጋብቻ ሕግ አንድ አካል የሆኑ ትን ሰዎች ለማለያየት ቢአስብም ቅሉ ፤ የአንዳቸ ውን ፊት ካላየ በስተቀር ፤ የጋብቻን ክብርና ጥቅም አውቀው ፤ በጨዋነት አጥር ተጠብቀው በሚኖሩ ባልና ሚስት መካከል ተንኮለኛ ሰው በፍጹም አይገባም ።

ክረምት ሲጠሉት ፤ ያከብራል ።

ሰም ፡ የክረምት ብርዱ ፡ ጭቃው ፡ ዝናቡ ፡ ጕርፉ ፡ የሚጠላና የሚያንገፈግፍ ቢሆንም እንኳ ፤ ክረ ምት ባበቀለው እህል ፡ ባጸደቀውም ተክል ገበሬን ያከብረዋል ።

ወርቅ ፡ ወላጆችና መምህራን ፡ ቅጣታቸው ፡ ተግሣጻ ቸው ፡ ቁጣቸው ፡ ለጊዜው እንደ ኮሶ ቢመርም እንኳ ፤ የድካማቸው ፍሬ ፡ የልጆቻቸውን ኑሮ ያሳምረዋል ።

ከቁንጫ ፡ መላላጫ ።

ሰም ፡ ተፈጥሮ በገላ መጠን ፡ ወይም በአቋም ፡ ሁሉንም ፍጥረት እኩል ስለማያደርግ ፤ በሰው ሠራሽ ጥበብ ይቅርና ፡ ትልቅ ተአምር እንኳ ቢደረግ ከትንሽዋ ፍጥረት ከቁንጫ ላይ የዶሮን ያህል መላላጫ ኩዶ አይገኝም ።

ወርቅ ፡ ገንዘብን ከኪሱ አውጥቶ ለድኾች እንዳይሰጥ እጁን የታሠረ ፡ ዓይኑንም የታወረ ከመሆኑ የተ ነሣ አስተዛዝነው ቢለምኑም ፤ ከቅርታም ሰው ዘንድ የገንዘብ ምጽዋት ይቅርና ፡ ቁራሽ እንጀራ እንኳን ምንም አይገኝም ።

ንም ቁርጥምጥም አድርጎ መብላት ለሚችለው ለአንበሳ ግን ሥጋን መስጠት ይገባል ።

ወርቅ ፡ ቢማርም እንኳ ፤ በአእምሮ ገና ላልበሰለና የሥራ ልምምድም ለሌለው ለጎረምሳ በበታችነት ዝቅተኛ ሥራ ብቻ መስጠት ነው ፤ በዕውቀት ለደረጀ በዕድሜ መስተዋት ብዙ ነገርን ላየ ለሸማግሌ ወይም ለጐልማሳ ግን በበላይነትና በኃላፊነት ከፍተኛ ሥራን መስጠት የተገባና የተፈተነም ነው ።

ከላይ ከደፈረሰ ከታች አይጠራም ።

ሰም ፡ ወራጅ ወይም የምንጭ ውሃ ከላይ ባለው ቦታ በአንድ ምክንያት ከደፈረሰ ዘንድ ፤ ከታች በሚገኘው ሥፍራ ላይ ምንም አይጠራም ።

ወርቅ ፡ በአስተሳሰብም ሆነ በአሠራር ከአባትና ከእናት መልካም አርአያ ካልታየ በስተቀር ፤ ከልጆች ዘንድ የባሰ ይሆናል እንጂ ፤ ለማኅበራዊ ኑሮ የሚጠቅም ለሀገርም የሚበጅ ተግባር ከቶ አይገኝም ።

ወርቅ ፡ ከሁሉ በላይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ካልተፈቀደ በስተቀር ፤ ከሰማይ በታች ለመበል ጸግም ሆነ የሕዝብም መሪ ለመሆን ምንም ቢሠሩና

በውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም ።

ሰም ፡ ጌታው ፡ ቅቤን ቢያጠጣው ፤ ወይም ሰርቆ ቢበላው ፤ ቅቤ ወዲያው ይወጣል እንጂ ፤ በውሻ ሆድ ውስጥ አይውልም ፤ አያድርም ።

ወርቅ ፡ ቢአስፈራሩትም ፤ ወይም ቢአባብሉትም እንኳ ፤ ምሥጢር በውሸታምና ትዕግሥት በሌለው ሰው ሆድ ውስጥ ፡ በጥብቅ ተይዞ ፡ ወይም ተጠብቆ ለብዙ ጊዜ አይኖርም ።

ወጥን ማን ያውቃል ፡- ቀላዋጭ ።

ሰም ፡ ወጥን ማን አሳምሮ ያውቃል ፡- ብዙ ዓይነት ወጦችን በየቤቱና በየድግሱ እየዞረ ብዙ ጊዜ የበላ ቀላዋጭ ሰው ነው ።

ወርቅ ፡ የማስተማርን ዘዴና የተማሪዎችን ጠባይ ማን በጣም ያውቃል ፡- በማስተማር ሥራ ለብዙ ዓመታት የቆየና እንዲሁም ልዩ ልዩ ጠባይ ካላቸው ተማሪዎች ጋራ ብዙ ጊዜ አብሮ የኖረ ነባር አስተማሪ ብቻ ነው ።

ወተት ለአንበሳ ፡ ሥጋ ለአንበሳ ።

ሰም ፡ ሣርን መብላት ገና ላልጀመረ ለአንበሳ ወተትን ብቻ መስጠት ነው ፤ ሥጋውን ድቅቅ ፡ አጥንቱ

ከሁለት ቅርንጫፍ ያረፈች ወፍ ፡ ፪ ክንፏን ትነደፍ ።

ሰም ፡ ከሁለት ቅርንጫፎች ላይ ያረፈች ወፍ ፡ ለመ ብረር በምትነሣበት ጊዜ ፤ ሁለት ክንፎችዋን ትነደፋለች ።

ወርቅ ፡ በመዋጋትና ሸሽቶ በማምለጥ መካከል ላይ መንታ ሐሳቡን ያሳረፈ ወታደር ፡ ከሁለት አን ዱን ሳይዘው ፤ በተማረከ ጊዜ ፤ ቆርጦ ባለ መዋ ጋቱ ፡ ወይም ሸሽቶ ባለማምለጡ ፡ ሲጸጸትና ሲያፍር ይኖራል ።

ወደሽ ከተደፋሽ ፤ ቢረግጡሽም አይክፋሽ ።

ሰም ፡ ብዙ ሰው ተጨናንቆ በሚወጣበት በር ላይ ወደሽ ድፍት ካልሽ ዘንድ ፤ እየተገፋፋ የሚወጣውም የሚገባውም ሁሉ ቢረግጥሽም ፤ መክፋት ወይም ማማረር የለብሽም ።

ወርቅ ፡ ጥፋትሽን እንድትተይ ፡ ጉድለትሽንም እንድ ታሚዱ ዘመድ ፡ ወዳጅ ቢመክርሽና ቢያስጠነ ቅቅሽ ፤ እንቢ ብለሽ ፡ ያንኑ የለመደብሽን አመል ስትቀጥዪ ፤ ቅጣት ፡ ወይም ጉዳት ፡ ቢደ ርስብሽ ፤ በደስታ መቀበል አለብሽ እንጂ ፤ዕድ

ቢፍጨረጨሩ ፤ ይፈጸማል ፤ ማለት ከንቱ ድካም ብቻ ነው ።

ከቅርብ የወደቀ ፡ ከቀ·ስል ዳነ ።

ሰም ፡ አወዳደቅ ፡ የተለያየ ሁኔታ ስላለው ፤ ከቅርብ ቦታ ላይ የወደቀ ሰው ፡ ምንም እንኳ ለጊዜው ቢያመውም ቅሉ ፤ ከቀ·ስል ይድናል ።

ወርቅ ፡ የቅጣት መጠን በወንጀሉ ስለሚለካ ፤ የበደል ሥራ የተለያየ ደረጃ አለው ፤ ስለዚህ ፡ አነስ ተኛ ጥፋት ያጠፋ ፡ ቢቀጣም ቅሉ ፤ ለብዙ ዓመታት ተፈርዶበት ከመታሠር ይድናል ።

ከወገኑ የተለየ አንበጣ ይሆናል ፌንጣ ።

ሰም ፡ ከወገኑ ፡ ወይም ከመንጋው ተለይቶ በአንድ ቦታ ላይ ተባራሪ ሆኖ የቀረ አንበጣ ፡ በገበሬ ዎች ዘንድ ፡ ከፌንጣ ተቆጥሮ ይናቃል እንጂ ፤ አዝመራን ያጠፋል ተብሎ ፡ አይፈራም ።

ወርቅ ፡ ከትውልድ ሀገሩ በአንድ ምክንያት ወጥቶ ፡ ከዘ መዶቹም ተለይቶ በሰው አገር ላይ የሚኖር ሰው ባይተዋር ይሆናል ። ማንንም አምኖ ስለማይ ጠጋም ፤ ብቸኝነት ይሰማዋል ።

ልሽን መራገም ፡ ዘመዶችሽንም ማማረር ከቶ አይገባሽም ።

ያመኑት ፈረስ ፡ ይጥላል ከደንደስ ።

ሰም ፡ ያመኑት ፈረስ ፡ ምንም እንኳ ፡ አሳድገው ፡ ገርተው ፡ እየመጨኑ በደኅና ቢይዙትም ፤ በጣም ከመጥገቡ የተነሣ ፡ ልቡን ሲነሣው ፤ አንድ ቀን ጌታውን ከደንደስ ላይ ክፉኛ መጣሉ አይቀርም ።

ወርቅ ፡ ብዙ ጊዜ ሳይታወቅበት ያለ ምሕረት የሚጐዳው ፡ ባልሆነ ቦታና ጊዜም ፡ በጭካኔ የሚጥለው ፡ ያመኑትና የወደዱት ሰው ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ወዳጅነቱን በማየት በብዙዎቹ ሰዎች ዘንድ ስለማይጠረጠር ነው ።

ዶሮ ብትታመም ፤ በግ አረዱላት ።

ሰም ፡ በአንድ ብር ከሰባዓ አምስት ሳንቲም የምትገዛ ዶሮ ፡ ብትታመም ፤ ቤዛ (ጭዳ) ይሆናት ዘንድ ወይም በሷ ፈንታ ተተክቶ እንዲሞት ዋጋው ጎምሳ ብር የሆነ በግን አረዱላት ።

ወርቅ ፡ ግምቱ ከሁለት ብር በማይበልጥ ጸብና ክርክር እንዲሁም ንዴትና እልህ ምክንያት ፤ ብዙ የሥራ ጊዜ ከመባከኑም በላይ ግርምቢጥ በሺሕ የሚቈጠር ብር ወጣ ። ይወጣልም ።

እንኳን ዘንቦብሽ ፡ እንዲያውም ጨዛ ነሽ ።

ሰም ፡ ልብስሽ በሙሉ እስቲበሰብስ ድረስ ፤ እንኳን ዝናብ ድንገት እላይሽ ላይ ዘንቦብሽ ይቅርና እንዲያውም ጨዛ (ቀዝቃዛ) ነሽ ።

ወርቅ ፡ አብዛኛው የሰው ልጅ እንኳን ተጣልተውት ፡ ምክንያት አግኝቶ ይቅርና ፡ እየወደዱትም ቢሆን የማንንም ስም ሆነ ብሎ ማጉደፍ ልማዱ ነው ።

አይጠቅም ጠላ ፡ ባልና ሚስት አጣላ ።

ሰም ፡ በሌላ ቀን ሁለተኛ የማይደገም ኃይለኛ ጠላ ፡ ደኅና ተስማምተው ይቀመጡ የነበሩትን ባልና ሚስት አሰከረና ክፉኛ አጣላ ።

ወርቅ ፡ እስተወዲያኛው የማያዛልቅና ለምንም የማይረባ ነገር ሁሉ ወዳጅን ከወዳጁ ፡ የበታችን ከበላዩ ፡ ሚስትን ከባልዋ ጋራ ሲያቈራርጥ ሲያለያይ ይኖራል ።

ወርቅ ፡ ከፍላጎቱና ከደስታው ጋራ ፡ በቅፅበት እንዳል ነበረ ሆኖ የሚያልፈው ዓለም ፡ ሰውን በማይረባ ነገር እያታለለ ፡ የማያልፈውን መንግሥት ሰማያትን ያሳጣል ።

አህያ ፤ ልጆችዋን ይዛ ብትጠፋ ፤ ዥብ የሚደፍራት አይመስላትም ።

ሰም ፡ አህያ ውርንጭላዎችዋን (ልጆችዋን) አስከትላ ከጌታዋ ዘንድ ብትጠፋና ፤ ወደ ጫካም ብትገባ ፤ ጨካኝ ጠላትዋ ዥብ የሚደፍራት አይመስላትም ።

ወርቅ ፡ ብድር መክፋፈል ፡ የማይቀር መሆኑን የሚዘነጋ ሰው ፡ በራሱ ትልቅነትና በወገኖቹም ተመክቶ ፡ ግፍ ቢሠራ ፤ ጡር ቢናገር ፤ ፍዳው ፡ ወይም ሞት ፡ ቀኑን ጠብቆ ፡ የሚደርስበት አይመስለውም ።

የአዳኝ ውሻ ፡ ትርፉ ፡ ፀጉር ባፉ ።

ሰም ፡ አዳኝ ውሻ ፡ እያደነ የያዘውን አውሬ ለጌታው ማስረከብ ስለአለበት የሱ ትርፉ ወይም ዋጋው የያዘውን አውሬ ፀጉር በአፉ መቅረቱ ብቻ ነው።

ወርቅ ፡ አያገባው ገብቶ ባልና ሚስትን የሚያጣላ ሰው የጎላ ጎላ በስብቀቱ ያጣላቸው ባልና ሚስት ሲታረቁ ፤ ለእሱ የሚያትርፈው ፡ ቂምና በቀል ብቻ ነው ።

ይገርማል ! አህያና ዥብ ፡ አብሮ ይከርማል !

ሰም ፡ አህያና ዥብ በዱና ተበዱ ፡ ወይም አጥፊና ጠፊ ሲሆኑ ፤ አንድ ላይ መክረማቸው ፡ በጣም የሚገርም ነው !

ወርቅ ፡ በአንዱ ሰው ፡ ልብ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ሌላው ሊያአውቀው ካለመቻሉ የተነሣ ፡ ያላወቀ ሰው ወዳጁ መስሎት ከጠላቱ ጋራ አብሮ መኖሩ ፡ በጣም ይገርማል !

ዶሮ ፡ ጭራ ጭራ ፡ ታወጣለች ካራ ።

ሰም ፡ ዶሮ ፡ ደመ ነፍስ እንጂ ፤ አእምሮ ያላት ፍጥረት ካለመሆንዋ የተነሣ ፡ የምትለቃቅመውን ለማግኘት ስትል ፤ እየጫረች ፡ የምትታረድበትን ካራ ታወጣለች ።

ወርቅ ፡ ሰው ፡ የብልግና ፍላጎቱን ለመፈጸም ሲል «አታመንዝር» የተባለውን ትእዛዝ እየጣሰ በሥጋው የሚቀጣበትን የመነካካት በሽታ በራሱ ላይ ያመጣል ።

ከወገብ በላይ ታቦት ፡ ከወገብ በታች ጣዖት ፤

ሰም ፡ ከወገብ በላይ ታቦት ፡ ከወገብ በታች ፡ ጣዖት ሆኖ የተሠራ ምስል ቢኖር ፤ በሱ ላይ ያሉት ሁኔታዎች ፡ ተቃራኒዎች ናቸው ።

ወርቅ ፡ ባንድ በኩል ሰውን በሕይወቱ ሳለ ፤ ለመቅበር ጉድጓድን እየቆፈሩ ፡ በአንድ ፊት ደግሞ ወዳጅ ለመምሰል እህል ውሃ የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ ፤ በነሱ የሚፈጸሙ ተግባሮች የማይስማሙ በመ ሆናቸው ፡ የክርስቲያን ሥራዎች አይደሉም ።

ባለቤቱ ፡ ካልጮኸ ፡ ጐረቤት ፡ አይረዳም ።

ሰም ፡ የሌባን መምጣት ሰምቶና አይቶ ወዲያው ባለ ቤቱ ፡ ካልጮኸ በስተቀር ፤ ጐረቤት ፡ የሆነ ውን ነገር ስለማያውቅ ፤ ፈጥኖ ሊረዳ አይች ልም ።

ወርቅ ፡ አሠሪ ወይም ቀጣሪ ሥራውን በቅርብ እየተከ ታተለ ካላሠራ በስተቀር ፤ ሠራተኞች ተቀጣ ሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ፡ ሥራውን እንደ ራሳቸው አድርገው ሊያከናውኑለት አይችሉም ።

ወርቅ ፡ በሽተኛ ወደ ሐኪም ዘንድ ኼዶ ፡ « እዚህ ላይ ያመኛል ፤ ይወጋኛል ፤ ያቃጥለኛል ፤ ወይም

የሚያመኝ ፤ ሆዴን ነው ፤ ራሴን ነው ፤ »ብሎ ካላመለከተ በስተቀር ፤ በሽታው ፤ በሐኪሙ ፍለጋ ብቻ በቶሎ ሊገኝለት አይችልም ።

ታሞ የተነሣ ፡ እግዚአብሔርን ረሣ ።

ሰም ፡ በጠና ታሞ ፡ ቆይቶ ፡ በኋላ ሲሻለው ከተኛበት አልጋ ላይ የተነሣ ሰው ፡ « የዛሬውን ማረኝ እንጂ ፤ ለወደፊቱ ግን ፡ ከቶ ከፈቃድህ አልወ ጣም ፤ » ይለው የነበረውን እግዚአብሔርን ፈጥኖ ረሳ ።

ወርቅ ፡ በድኽነት ሲቆራመድ ኖሮ ፤ ከጊዜ በኋላ ያለ ፈለት ሰው ፡ « አምላኬ ሆይ ! ከዚህ ከድኽነት ብታላቅቀኝ ፤ ችግረኞችን እረዳለሁ ፤ ባጭሩም እንደ አብርሃም እሆናለሁ ፤ » እያለ ይለምነው ይሳለው የነበረውን እግዚአብሔርን ወዲያው ከዳ ።

ትንሽ ቆሎ ይዛ ፡ ካሻሮጋ ትጠጋ ።

ሰም ፡ አጭበርባሪ ልጅ ፡ ተመልካቹን ለማደናገር እን ዲመቻት ፡ ጥቂት ቆሎ ይዛ አሻሮ አለበት ጋ ትጠጋለች ።

ወርቅ ፡ ብልጥ ሰው ፡ ወይም ብልጥ መንግሥት ፡ በረ ቀቀና አርቆ በሚመለከት ዘዴው ፡

ነብር የሞተ ለት ፡ ፍየል ልጅዋን ትድራለች ።

ሰም ፡ ነብር ፡ የጥንትም ፡ ያሁንም ፡ የወደፊትም አጥፊዋና ጠላትዋ ስለሆነ ፤ እሱ የሞተ ለት ፍየል በጫካ ውስጥም ቢሆን ፡ ልጅዋን በደስታ ትድራለች ።

ወርቅ ፡ ጦርነት የሰላም ተቃራኒና የሰው ልጆችም አጥፊ ጠላት ስለ ሆነ ፤ እሱ ከምድር ገጽ የተደመሰሰ ለት የመላው ዓለም ሕዝብ ያለ ሥጋት በምቾትና በደስታ በኖረ ነበር ።

ተቀምጦ የሰቀሉት ፡ ቆሞ ለማውረድ ያስቸግራል ።

ሰም ፡ ተቀምጦ የሰቀሉትን ዕቃ ፡ እንደገና ቁጭ ብሎና ሥራ ፈትቶ ካልሆነ በስተቀር ፤ ቆሞ ፡ ወይም ፈጥኖ ለማውረድ ያስቸግራል ።

ወርቅ ፡ ልብ በሰብአዊ ርኅራኄ ሲነካና ሲሸነፍ ፤ለሰው ያበደሩትን ፡ ብዙ ገንዘብ በውሉ መሠረት በሰላምና በፍቅር ተመልሶ ለመቀበል ያስቸግራል ።

ወርቅ ፡ በንዴት ወንበር ላይ ተቀምጦ ፡ ከፈጸሙት መጥፎ ተግባር ፡ ወይም አስቀድሞ መልሱን ሳያሰናዱ ፤ ድንገት ከተናገሩት ነገር በደኅና ለማምለጥ በጣም ያስቸግራል ።

አጠፋታውን ለመዝረፍ ፡ ያዘነ መስሎ አስቀድሞ ትንሽ ርዳታ ይዞ አንዱጋ ጠጋ ይላል ።

አንበሳ የሰበረው ፡ ለኾብ ይተርፈው ።

ሰም ፡ አንበሳ በልቶ ማብላት ልማዱ ስለሆነ ፤ አድኖ በማግኘት የሰበረው እንስሳ ለሰነፉና ለደካማው ለፈሪውና ለሆዳሙ ለኾብ ይተርፈዋል ።

ወርቅ ፡ አርበኞች ደማቸውን አፍሰው ፡ አጥንታቸውን የትም ከስክሰው ያስገኙት ነፃነት ለማንም ይተርፈዋል ።

አንተም ሌባ ፤ እኔም ሌባ ፤ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ ፡-

ሰም ፡ አንተም ሌባ ነህ ፤ እኔም ሌባ ነኝ ፤ ታዲያ ያጋጠመንን ነገር ተስማምተን ለሁለት ሰርቀን ከቦታው ላይ ጥፍት እንደ ማለት ፈንታ ፡ በሰው ገለባ ምን ያጣላናል ፡-

ወርቅ ፡ እኔና አንተ ፡ በዚህ ዓለም ላይ በአንድነት ለጥቂት ጊዜ ቆይተን እንደ ጥላ ከነበርንበት ቦታ ላይ የምናልፍ ፡ ወይም የምንዛወር ስንሆን ፤ተስማምተንና ተረዳድተን በመኖር ፈንታ ጥለነው በምንኼደው ነገር ሁሉ ምን ያፋጅናል ፡-